# ስለ የፋሺሽት ኢጣልያ የጦር ወንጀልና ለአድዋ ድል በቀል ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ

ኪዳኔ ዓለማየሁ

**ዋና ነጥቦች፤**

- ስለ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ፍላጎት፤
- ስለ ውጫሌ ውልና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ውጤት፤
- ስለ አድዋ ድልና ስላስከተለው የበቀል ጦር ወንጀል፤
- ስለ ቫቲካን ሚና፤
- ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ።

**የውጫሌ ውል**

አጼ ምኒልክና የኢጣልያው ተወካይ፤ ፒየትሮ አንቶኒሊ፤ የውጫሌውን ውል የተፈራረሙት ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ/ም

1. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ “ዐጼ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት”፤ 1983፤ ገጽ 46
2. ፔትሪዲስ፤ ኤስ. ጴጥሮስ፤ “የአድዋው ጀግና የልዑል ራስ መኮንን ታሪክ” 1961፤ ገጽ 86-87




በደጃች መኮንን (በኋላ ልዑል ራስ) መሪነት ኢጣልያ የተጓዙት የኢትዮጵያ ልዑካን

<u>**የጉብኝቱ ውጤት፤ የውጫሌው ውል ያስከተለው ጠንቅና የአድዋው የኢትዮጵያ ታላቅ ድል፤**</u>

በጊዜው፤ በደጃች መኮንን የተመራው የመልእክተኞች ቡድን ዓላማው ተሳክቶለት በተከናወነው ተጨማሪ ስምምነት 4 ሚሊዮን ሊሬ ብድር (6) ከተገኘ በኋላ 28 ባለሰባ ሚሊ ሜትር ጠመንጃዎች፤ 38 000 ጠመንጃዎችና 2 500 000 ጥይቶች የሚገኙበት የጦር መሣሪያ ለመግዛት ችለው፤ ጉዟቸውን አጠናቅቀው፤ በኢየሩሳሌም በኩል ወደ ሐገር ተመለሱ።

ጳውሎስ ኞኞ እንደ ጻፈው፡

> "....በኢጣልያ አገር ሰዕል እንዲማሩ ተልከው የነበሩት ልጅ አፈወርቅ ገብረየሱስ (በኋላ ፕሮፌሰር የሆኑት) በጋዜጣ
> ያነበቡትን ለራስ መኮንን ነገሩዋቸው። ራስ መኮንንም አስጎብኚያቸው የነበረውን አንቶኒሊን ቢጠይቁት "........ያ ደደብ
> ኢትዮጵያዊ ተማሪ ትርጉም ስላልገባው ነው" ብሎ ተሳደበ። ራስ መኮንንም ተቃውሞዋቸውን
> ለኢጣሊያ መንግሥት አሳወቁ ከነገሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የውሉን መበላሸት ለአጤ ምኒሊክ
> አሳወቁ።"

ስለ አድዋው ድል በጊዜው ከተደረሱት ግጥሞች መሀል፡

“ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ
ግብሩ እንቁላል ነበር ይኸን ጊዜ አበሻ።
በሠራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ
ተፈጠመ ጣልያን አበሻ እንዳይደርስ።
መድፉን መትረየሱን ባድዋ መሬት ዘርቶ
እንክርዳዱን ነቅሎ ስንዴውን ለይቶ
የዘራውን እህል አጭዶና ወቅቶ
ላንቶኒሊ አሳየው ፍሬውን አምርቶ።
እንዳቀና ብሎ ሰለምኖ መሬት
ንግድ ሊያሰፋበት ሊዘራ አትክልት
እየመጣ ሊሰጥ ግብሩን ለመንግሥት
ለጓዙ ማረፊያ አገር ቢሰጡት
ተጠማኝ ሰንብቶ ሆኖ ባለርስት
ወሰን እየገፋ ጥቂት በጥቂት
እውነት እርስት ሆነው ተቀበረበት።
ባሕር ዘሎ መምጣት ለማንም አትበጅ
እንደ ተልባ ስፍር ትክዳለች እንጂ
አትረጋምና ያለተወላጅ።”

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ “አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት”፤ 1983፤ ገጽ 506

# የየካቲት 12 የሰማእታት ዝክረ በዓል

ስለ የፋሺሽት ኢጣልያና የቫቲካን የጦር ወንጀልና ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ

1ኛ/ <u>የፋሺሽት ኢጣልያ የጦር ወንጀል</u>



የኢጣልያ ፋሺሽት ወታደሮች የኢትዮጵያዊውን ራስ ቆርጠው ሲያሳዩ



ፋሺሽቶች በመርዝ ጋዝ የተጨፈጨፉትን የኢትዮጵያውያን ሬሳዎች ሲመለከቱ

1 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል፤

ከነዚሁ ውስጥ በየካቲት 12-14 ሶስት ቀኖች ውስጥ 30000 ኢትዮጵያውያን፤
አብርሃም ደሞዝ፤ ሞገስ አስገዶም፤ ሮዶልፎ ግራዚያኒ፤ ጉዊዲ ኮርቴዜ
ከዚያም፤ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከ2000 በላይ መነኮሳትና ምእመናን፤

እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን በመርዝ ጪስ፤ በስቅላት፤ ራስን በመቅላት እንዲሁም በብትር ጫፍ ላይ ሰክቶ በማሳየት፤ ሰውን በሕይወት እያለ ከአውሮፕላን በመወርወር፤ ቤተሰቦችን ሕጻናትን ጭምር ከነቤቶቻቸው በማቃጠል፤ በእስር፤ በግርፋት፤ በስደት፤ በዝርፊያ፤ በዘር ልዩነት፤ ወዘተ ተጨፍጭፈዋል/ተሰቃይተዋል። (Ian Campbell, “The Addis Ababa Massacre – Italy’s National Shame”)

2000 ቤተ ክርስቲያኖች፤ 525000 ቤቶችና 14 ሚሊዮን እንስሶች ወድመዋል።

እጅግ ብዙ የኢትዮጵያ ንብረት ተዘርፏል፤

አንዳንድ ፋሺሽት ዘራፊዎች፤
ባዶሊዮ (Badoglio) 300 ሻንጣዎች፤
ግራዚያኒ (Graziani) 79 ሻንጣዎች፤
ቴሩዚ (Teruzi) በ300 ከባድ መኪናዎች።
የአክሱም ኃውልትም ተዘርፎ በኋላ ተመለሰ።
**500 ታሪካዊ የኢትዮጵያ ሰነዶች ባሁኑ ጊዜ በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ይገኛሉ።**

- በጊዜው፤ በዓለም ሕግ በተከለከለ የመርዝ ጋዝ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተጨፈጨፉ፤
  - Town Date of attack
- Takkaze 22 Dec. 1935
  - Amba Alaa 26 Dec. 1935
  - Borena 31 Dec. 1935
  - Sokota 10 Jan. 1936
  - Makale 21 Jan. 1936
  - Megalo Feb. 1936*a*
  - Waldia Road 27 Feb. 1936
  - Quoram 16 Mar. 1936
  - Ylanserer 17 Mar. 1936
  - Quoram 17–18 Mar. 1936
  - Irga Alem (Yirgalem)19–21 Mar. 1936
  - Indomahoni 29–30 Mar. 1936
  - Quoram 4–7 Apr. 1936
- Grip, Lina and Hart, John, “The Use of Chemical Weapons in the 1935-36 Italo-Ethiopian War”

በኢትዮጵያና በኢጣልያ በኩል ተሰልፈው የነበሩት ኃይሎች፤

**<u>በኢጣልያ በኩል</u>፤**

685000 ከኢጣልያ የመጡ ወታደሮች፤
ከኤርትራና ከሶማልያ ያስመጧቸው ከ600000 ወታደሮች፤
9300 መትረየሶች፤ 2275 ከባድ መሣሪያዎች፤ 799 ታንኮችና 595 አውሮፕላኖች፤
በሌሎች የጦር መሣሪያዎች፤ ለምሳሌ፤ በቦምቦች፤ በመርዝ ጋዝ፤ በስቅላት፤ በእስራት፤ በእሳት በማቃጠል፤
ከከፍተኛ ቦታና ከአውሮፕላን በመወርወር፤ በጩቤ፤ በዶማ፤ በዘረኛነት በማግለል፤ ወዘተ ተጠቅመዋል።



“የኢትዮጵያ ጨፍጫፊው” ሮዶልፎ ግራዚያኒ

ግራዚያኒ ለሙሶሊኒ ገብቶ የነበረው ቃል ኪዳን፤
“ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያውያን ጋር ወይንም ያለኢትዮጵያውያን አስረክብሀለሁ።”
(“I will deliver Ethiopia with or without Ethiopians”)



በመርዝ ጋዝ የተጨፈጨፉ ኢትዮጵያውያንና ፋሺሽት ኢጣልያኖች

**<u>በኢትዮጵያ በኩል፤</u>**

350 000 – 760 000 የጦር ሠራዊት፤

400 000 ያረጁ ጠመንጃዎች፤

234 ከባድ መሣሪያዎች፤

75 የታንክ ማጥቂያ ከባድ መሣሪያዎች፤

4 “ፊያት” ታንኮች (የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ዓይነቶች)፤

13 ጊዜው ያለፈባቸው አውሮፕላኖች ከ4 አብራሪዎች ጋር።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጦርነቱ ላይ




ራስ አበበ አረጋይ



በላይ ዘለቀ



የአቡነ ጴጥሮስ ኃውልት



አቡነ ሚካኤል




የሴት አርበኛ  ወ/ሸዋረገድ ገድሌ




ሲልቪያ ፓንከርስት ከጃንሆይ ጋር



ራስ ጌታቸው ከሙሶሊኒ ጋር



ለኢትዮጵያ ተዋግቶ የነበረው አሜሪካዊው ኮሎኔል ጆን ሮቢንሰን (Col. John Robinson)



ሙሶሊኒና የሴት ወዳጁ ተገድለው በዝቅዝቅ እንደ ተሰቀሉ

2ኛ/ <u>የቫቲካን ሚና፤</u>



የቫቲካኑ ፖፕ ፓየስ 11ኛ



እ.አ.አ. በ1926 ሙሶሊኒና የፖፕ ፓየስ 11ኛ ተወካይ፤ አቡነ ጋስፓሪኒ "ላተራን" የተሰኘውን ውል ሲፈራረሙ

**<u>በኢትዮጵያ ላይ በተፈጸመው የጦር ወንጀል ቫቲካን ከፋሺሽት ኢጣልያ ጋር ስለ መተባበሯ ማስረጃዎች፤</u>**

- የካቶሊክ ፓርቲዋን አስወግዳ ለፋሺሽት ፓርቲው እውቅና መስጠቷ፤
- ሙሶሊኒ ለቫቲካን ፲.5 ቢሊዮን ሊሬ እርዳታ መስጠቱ፤
- ብዙ የካቶሊክ ሊቃነ ጳጳሳት፤ ጳጳሳትና ካሕናት ወርቆቻቸውን ለፋሺሽቱ ጦርነት ማበርከታቸው፤
- ፖፕ ፓየስ ፲፩ኛ የኢጣልያኑን ንጉሥ፤ "የኢጣልያ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" በማለት መባረካቸው፤ **<u>(New York Times, Feb. 13, 1937)</u>**
- አጼ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣናቸውን ለኢጣልያ እንዲለቁ በቫቲካን በኩል ፩ ሚሊዮን ስተርሊንግ ፓውንድ ጉቦ ሊሰጧቸው መሞከራቸው፤
- የቱራና ካቶሊክ ጳጳስ ስለ ጦርነቱ ሲናገሩ፤ "ከሀዲ" ("schismatics") ኢትዮጵያውያንን ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀየሩ ስለሚረዳ ቅዱስ ጦርነት (crusade) መሰኘት አለበት ማለታቸው፤
- የፋሺሽቱ ኢጣልያ ጦር አዲስ አበባ ሲገባ ደስታቸውን ከገለጹት የዓለም መሪዎች ውስጥ ፓፕ ፓየስ ፲፩ኛ አንደኛው መሆናቸው፤
- የካቶሊክ ካሕናት የፋሺሽት ኢጣልያዊውን ጦር መባረካቸው፤



የካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን ካሕን የፋሺሽት ኢጣልያን ጦር ሲባርኩ

- ፋሺሽት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ስለ ፈጸመችው የጦር ወንጀል ቫቲካን ምንም ተቃውሞ አለመግለጿ።

**3ኛ/ <u>በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል ተጠያቂዎቹ፤</u>**

- የኢጣልያ መንግሥት፤
- ቫቲካን፤
- የእንግሊዝ መንግሥት፤
- የፈረንሳይ መንግሥት፤
- የአሜሪካ መንግሥት፤
- የዓለም መንግሥታት ማሕበር (League of Nations);

4ኛ/ **<u>የፋሺሽት ኢጣልያ የጦር ወንጀል ፍጻሜና የፍትሑ ሁኔታ፤</u>**

- በኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ትግልና በእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ
- ኢጣልያ ለሁለተኛ ጊዜ ተሸንፋ ተወገደች፤
- በኢጣልያ በኩል የአክሱምን ኃውልት ከመመለስና ለቆቃ ግድብ
- ከሰጠችው ኢምንት $25 ሚሊዮን እርዳታ ሌላ ምንም ያከናወነችው ነገር የለም፤
- በተቃራኒው፤ የኢትዮጵያ ጨፍጫፊ (“butcher of Ethiopia”) በመባል ለሚታወቀው፤ ለሮዶልፎ ግራዚያኒ፤ የጀግንነት መታሰቢያ አፊሌ በምትባል የኢጣልያ ከተማ ተመርቆለታል።

5ኛ/ **የአውሮፓ ምክርቤት መልስ**

**<u>ውድ ሐገራችን ኢትዮጵያ 82 ዓመት ሙሉ የሚገባትን ፍትሕ ሳታገኝ ቀርታለች። በኛ በልጆቿ ጥረት መብቷ የሆነውን ፍትሕ እንደምትጎናጸፍ ጥርጥር የለውም!</u>**



የቫቲካን ተወካይ በተገኙበት እ.አ.አ በ2012 የተመረቀው ለግራዚያኒ መታሰቢያ የተሠራው ኃውልት

- ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ካለመጠየቋ በላይ፤ በቤተ መጻሕፍቷ የሚገኙትን ከ500 በላይ የሆኑ የተዘረፉ ሰነዶች ለኢትዮጵያ አልመለሰችም።
- በተጨማሪም፤ ቫቲካን በቅርቡ ባሰራጨችው ጥናታዊ ፊልም በኃላፊነት የማትጠየቅ መሆኑ ተጠቁሙዋል። የብፁዕ አቡነ ማትያስና የካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ አስተያየት።
- ቫቲካን አይሑዶችን፤ የላቲን አሜሪካንና የሩዋንዳን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቃለች።

6ኛ/ **<u>አንዳንድ ሌሎች ሐገሮች ለፍትሕ ያከናወኑት ጥረት፤</u>**

- ሊቢያ፤ ለተጨፈጨፈባት 30000 ሰው 5 ቢሊዮን ዶላር ካሣ ለማግኘት ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ተዋውላለች።

- አርሚኒያ፤
    - በቫቲካን፤ በአሜሪካ መንግሥትና በአውሮፓ አንድነት ምክር ቤት በቱርኮች ስለ ተፈጸመባት የጦር ወንጀል እውቅና አግኝታለች፤
    - የአርመን ቤተ ክርስቲያን የተነጠቀችውን አንድ ገዳምና ደብር እንዲመለስላት የቱርክን መንግሥት በገዛ አገሩ ከሳለች፤
    - የአርመን ምሑራን ቱርኮች በፈጸሙባቸው የአንድ ሚሊዮን ሕዝብ ጭፍጨፋና ሌላም ወንጀል 3 ትሪሊዮን ዶላር ካሣ ጠይቀዋል። ካሣውም እየተጠየቀ ያለው ከቱርክ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ተጠያቂ ናቸው ከሚሏቸው ሌሎች መንግሥቶች ጭምር ነው።
    - በአሜሪካ ብቻ፤ ለፍትሕ የሚታገሉ ሁለት ማሕበራዊ ድርጅቶች አሏቸው።

- ናሚቢያ፤ በጀርመን መንግሥት ይቅርታ ተጠይቃ፤ 3 ቢሊዮን ዶላር ካሣ ጠይቀዋል። የጀርመን መንግሥት ላይ በአሜሪካ ውስጥ ሕጋዊ እርምጃ ወስደዋል።
- ኬንያ፤ በእንግሊዝ መንግሥት ይቅርታ ተጠይቀው ካሣ እየተከፈሉ ነው።
- ኢንዶኒዚያ፤ በኔዘርላንድስ መንግሥት ይቅርታ ተጠይቀው ካሣ እየተከፈሉ ነው።

# 7/ <u>ት ግ ል  ለ ፍ ት ሕ</u>

Global Alliance for Justice

The Ethiopian Cause

**<u>ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ</u>**

(www.globalallianceforethiopia.net)

7.1 **ዓላማ፤**

(ሀ) ኢጣልያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተገቢውን ካሣ እንድትከፍል፤ (በፕሮጀክት)

(ለ) ከኢትዮጵያ የተዘረፈው ንብረት እንዲመለስ፤

(ሐ) ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤

(መ) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በፋሺሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል እውቅና እንዲሰጥ፤

(ሠ) ለሮዶልፎ ግራዚያኒ በአፊሌ ከተማ፤ ኢጣልያ የተሠራው መታሰቢያ እንዲወገድ።

7.2 **የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች፤**

(ሀ) የፍትሕ አቤቱታዎች፤

- ለኢጣልያ መንግሥት፤
- ለቫቲካን፤
- ለአውሮፓ ምክር ቤት፤
- ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤
- ለዓለም መንግሥታት ማሕበር፤
- ለእንግሊዝ መንግሥት፤
- ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት፤
- ለኢትዮጵያ መንግሥት፤
- ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፤
- በፍትሕ ለሚያምኑ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች፤

(ለ) የየካቲት 12 ዓመታዊ ዝክረ-በዓል በ30 ከተሞች፤

- በጸሎት፤
- በጉባኤ፤
- በሰላማዊ ሰልፍ፤

- በየካቲት 12 ከሚዘከሩባቸው ሥፍራዎች ውስጥ በመጀመሪያ ያረጋገጡት በኢጣልያ በሮምና በቤሉኖ ከተሞች ስለሚከናወነው ነው።

(ሐ) በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀልና ስለሚያስፈልገው ፍትሕ በዶር. አሕመድ ሀሰን ጥናት እየተከናወነ ነው።

(መ) ስለ ግራዚያኒ መታሰቢያ የአውራጃው የፍርድ ቤቱ ሒደት፤

- የላዚዮ አውራጃ ምክር ቤት እንዲወገድ ወስኗል።
- የኢጣልያ ፍርድ ቤት በቅርቡ የበየነው፤




የአፊሌ ከተማ ከንቲባ፤ ኢቶሪ ቪሪና ከኋላው የሚታየው የግራዚያኒ ምስል

1ኛ/ የአፊሌ ከንቲባ፤ ኢቶሬ ቪሪ (Ettore Viri) የ8 ወሮች እስራትና የ120 ዩሮ (Euro) ቅጣት ተፈርዶባቸዋል።

2ኛ/ ሁለት የከተማው ምክር ቤት አባሎች፤ ፔፔሮኒ እና ፍሮዞኒ (Peperoni and Frosoni) እያንዳንዳቸው የ6 ወሮች እስራትና የ80 ዩሮ (Euro) ቅጣት ተፈርዶባቸዋል።

3ኛ/ ተከሳሾቹ ለ5 ዓመት ከመንግሥት ሥራ እንዲወገዱ ተፈርዷል።

4ኛ/ ተከሳሾቹ፤ የፋሺሽት ተቃዋሚ ለሆነው አንፒ (ANPI = Italian National Partisan Association) ለተሰኘው ድርጅት 8000 ዩሮ (Euro) እንዲከፍሉ ተፈርዷል።

5ኛ/ ክሱን ላቀረበባቸው መሥሪያ ቤት 1800 ዩሮ (Euro) እንዲከፍሉ ተፈርዷል።

Celebrazione per

# IL GIORNO DEI MARTIRI ETIOPICI



## Domenica 17 Febbraio 2019
## ore 16.00

presso

**teatro della scuola Di Donato** via N. Bixio n° 83 Roma.

Con la partecipazione di:

Gabriella Ghermandi,
Rappresentanti della Chiesa Ortodossa di Roma,
Rappresentante ANPI provincia di Roma,
Rappresentante dell' Ambasciata Etiopica.

Aderiscono: l'Ass. della Comunità Ethiopica in Italia; l'Ass IDIR e l'Ass Unione Etiopica a Roma.

Promosso da l'ARI
(Federazione Assemblee Rastafari in Italia)
ed EXODUS Ethiopian Cultural Service.

ANPI

# ጉዳዩ የሚያበረታታ ደረጃ ሲሆን፤ በይግባኝ እየታየ ነው።

(ሠ) የኢ.ኮ.ሶ.ክ (ECOSOC) አባልነት፤

(ረ) ዋሺንግተን ዲ.ሲ. የተከናወነው ዓለም አቀፍ ጉባኤ፤
(ሰ) ስለ ጦር ወንጀሉና ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ ያለው ግንዛቤ እየተጠናከረ መሆኑ፤

- እነቫሌሪዮ ቺሪያቺ (Valerio Ciriaci) ያሰራጩት ተደናቂ ጥናታዊ ፊልም፤
- እነቀሲስ/ዶር ምክረ-ሥላሴ ገ/አማኑኤል፤ ኢያን ካምፐቤልና (Ian Campbell) ኪዳኔ ዓለማየሁ የደረሷቸው መጻሕፍት፤ (የቀሲስና የኪዳኔ መጻሕፍት ለፖፕ ፍራንሲስ የተበረከቱ መሆኑ)፤
- እነካርሜሎ ቺሪያቺና ጌርማንዲ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ፤ ከፋሪ (FARI) እና አንፒ (ANPI) ከተሰኙ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የዚህን ዓመት የሰማእታት እለት የካቲት 10 ቀን 2011 ዓ/ም ሮም መዘከራቸው፤

(ሸ) በማሕበሩ ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘው፤ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ የሚያመለክተው አቤቱታ በ8700 ሰዎች በላይ (በኢጣልያኖች ጭምር) መፈረሙ፤ (የሚያስፈልገው ግን 100 000 መሆኑ)
(ቀ) በሐገር ሽማግሌዎች የመጠቀሙ ሒደት፤

- ዶር. ያዕቆብ ኃ/ማርያምና አቶ ጨፍቁ ደሣለኝ ስለ ካርዲናል ብርሃነየሱስ፤
- አቶ ሺመልስ አዱኛ፤ አቶ ከበደ ገ/ማርያም፤ ወዘተ. ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፤ የኢትዮጵያ አርበኞች ማሕበር፤ ወዘተ፤

(በ) በአቶ ዳንኤል ግዛውና በአቶ ብዙአየሁ እየተረዳ የሚገኘው ድረገጽ እየተሻሻለ መገኘቱ።

7.3 አንዳንድ የተከሰቱ ጉዳዮች፤

* በበጎው በኩል (በኢጣልያኖች በኩል የአውራጃው ግዛትና ፍርድ ቤትና የአንዳንድ ኢጣልያኖች)፤

* በሌላ በኩል (የካርዲናል ብርሃነየሱስና የብፁዕ አቡነ ማትያስ ገለጻዎች)፤

7.4 **<u>እቅድ</u>**

የማሕበሩ ዋናዎቹ እቅዶች፤

- ዓላማዎቹ እንዲሳኩ ጥረቱን ማጠናከር፤
- የተሻለ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
- ተሳትፎችን ማጠናከር፤
- አቤቱታውን ማጠናከር፤
- ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ የአቤቱታው ፊርማ ቁጥር 100 000 እንዲሞላ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፤
- ስለ ፋሺሽት የኢጣልያ የጦር ወንጀል ጥልቅ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ 2ኛውን ዓለም አቀፍ ጉባኤ በአዲስ አበባ ማከናወን፤
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች ለሐገር ስለሚያስፈልገው ፍትሕ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ መወትወት፤ በተለይ መንግሥት፤
- በተቻለ መንገድ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ፤
- የግራዚያኒ መታሰቢያ መወገዱን ማረጋገጥ፤

7.5 <u>ውድ ሐገራችን፤ ኢትዮጵያ፤ የሚገባትን ፍትሕ እንድትጎናጸፍ እንዴት ልንረዳ እንችላለን?</u>

(ሀ) ጉዳዩ የ እያንዳንዳችንን ኃላፊነትና ግዴታ የሚመለከት መሆኑን በመገንዘብ ዓላማዎቹ እንዲሳኩ መርዳት፤ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ አቤቱታውን መፈረምና ማስፈረም፤

(ለ) ለታቀደው ዓለም አቀፍ ጉባኤ በሀሳብ፤ በተግባርና በገንዘብ መርዳት፤

(ሐ) ወጣቶች ለሐገራችን ስለሚያስፈልገው ፍትሕ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

(መ) የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ ማስፈለጉ፤

(ሠ) የመገናኛ ብዙኃን እርዳታ ማስፈለጉ፤

(ረ) በየዓመቱ በሚከናወነው የየካቲት 12 ዝክረ-በዓል በብዛት መሳተፍ፤

(ሰ) በዋሺንግተን ዲ.ሲ. በኒውዮርክ፤ በአውሮፓና በኢትዮጵያ ግብረ ኃይሎች ማቋቋም፤

(ሸ) ለሐገራችን ክብርና ፍትሕ ሁልጊዜም ሳያሰልሱ መቆም!

7.6 አንድ ኢጣልያዊ አቤቱታውን ከፈረመ በሑዋላ ያቀረበው አስተያየት፤

I'm an Italian, born during this atrocity, and wish to express my profoundest horror that this was done by members of the government, who were from the country of my origins. No apology can possibly begin to deal with this inhumanity directed at the Ethiopian people. I'm filled with revulsion and sorrow at discovering the extent of the Italian governments involvement during the period of 1935-41, in these hideously inhuman actions.

7.7 “የኢትዮጵያ ልቅሶ” (በአቶ ሐዲስ ዓለማየሁ)፤

“ጀግና አልተተካም ወይ ፣ በቴዎድሮስ ስፍራ
ጎበዝ አልቆመም ወይ ፣ በዮሃንስ ስፍራ ፣
ሰው የለበትም ወይ ፣ በምኒሊክ ስፍራ ፣
ጠላቴ ሲወርረኝ ፣ ከቀኝ ከግራ ፣
የሚሰማኝ ያጣሁ ፣ ብጣራ ብጣራ ።
ወይ እኔ ኢትዮጵያ የጀግኖች እናት ፣
ሁሉም አለቁና ፣ ትተው ባዶ ቤት ፣
ደርሶብኝ የማያውቅ ፣ አገኘኝ ጥቃት ።
አሁን ጊዜው ሳያልፍ ፣ ካልተጋደላችሁ ፣

ቢጭኑት አጋሰስ ፣ ቢያርዱት ሰንጋ ናችሁ ።”

**<u>ቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ ለውድ ሐገራችን የሚገባውን ፍትሕ እንድናስገኝ ያበርታን!!</u>**